# በኢፌዴሪ ንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር

## የኢትዮጵያ ሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት

## የ2016 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት

ሰኔ 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

| ማውጫ | | ገጽ |
|---|---|---|
| ተ.ቁ | ርዕስ | |
| 1 | መግቢያ | 2 |
| 2 | ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም፣ የሀብት አጠቃቀም እና የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራር ማጎልበት ስራዎችን በተመለከተ | 2 |
| 3 | በቁልፍ የውጤት አመላካቾች ላይ የተመሰረተ የልማት ዕቅድ አፈጻጸም ትንተና | 3 |
| 4 | የዋና ዋና ተግባራት ጠንካራና ደካማ ጎን | 16 |
| 5 | ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ መፍትሔዎች | 17 |
| 6 | የ2016 በጀት ዓመት የሰው ኃይል መግለጫ | 18 |
| 7 | የ2016 በጀት ዓመት የፋይናንስ አፈጻጸም | 19 |
| 8 | ማጠቃለያ | 20 |
| 9 | የ2016 በጀት ዓመት የዋና ዋና ግቦች አፈፃፀም በሠንጠረዥ | 22 |

1. መግቢያ

የኢትዮጵያ ሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት ከ2016-2018 የኢንስቲትዩቱን ስትራቴጂክ ዕቅድ መሰረት በማድረግ፣ በ2015 በጀት ዓመት ያልተጠናቀቁ ተግባራትን በማካተት የ2016 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ስድስት ወራት አፈጻጸም በመገምገም ዕቅዱ ተከልሶ ወደ ትግበራ ተገብቷል፡፡ በዚሁ መሠረት በ2016 በጀት ዓመት በበጀት ዓመቱ ውስጥ የተከናወኑ የዋና ዋና ተግባራት አፈጻጸም፣ ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም፣ የሀብት አጠቃቀም፣ የአገልግሎት አሰጣጥ ስራዎች፣ በቁልፍ የውጤት አመላካቾች ላይ የተመሰረተ የልማት ዕቅድ አፈጻጸም ትንተና፣ በአፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ ተግዳሮቶች፣የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች እና ማጠቃለያ በማካተት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

2. ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም፣ የሀብት አጠቃቀም እና የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራር ማጎልበት ስራዎችን በተመለከተ

የኢትዮጵያ ሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት ላቦራቶሮችና ዎርክሾፖች በፋሲሊት ለማደራጀት አሁን ላይ በንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚ/ር በኩል በመከናወን ላይ ያሉ ለላብራቶሮች፣ ለወርክሾፖች እና ለቢሮዎች ግልጋሎቶች የሚውሉ ስድስት ከ5 እስከ 6 ወለል ያላቸው ህንጻዎች በመገንባት ላይ ናቸው፡፡ በተጨማሪም በጥራት መሰረተ ልማት ፕሮጀክት በአለም ባንክ ብድር የተለያዩ መሳሪያዎች የተገዙና ቀሪዎቹ ደግሞ በግዢ ሂደት ላይ በመሆናቸው በመካከለኛ የልማት ዕቅድ ዘመን ተጠናቀው የሥነ-ልክ ተቋምን አቅም በማሳደግ ለአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ ስኬት ከምርታማነት ጥራትና ተወዳደሪነት አንፃር ኢንስቲትዩቱ ዓይነተኛ ሚናውን መጫወት እንደሚያስችሉት ይጠበቃል፡፡

በሌላ በኩል የኢንስቲትዩቱ ማቋቋሚያ ደንብ ጸድቆ ስራ ላይ ከዋለ አስራ ሁለት ዓመታትን ያስቆጠረና በአፈጻጸም፣ በአደረጃጀት፣ በተጠሪነት እና በመሰረታዊ ስልጣንና ተግባር ረገድ ውስንነቶች ያሉበት በመሆኑና ይህንንም በመቅረፍ በዘርፉ የሃገሪቱ ፍላጎት አሁን ከተደረሰበት ደረጃ ጋር ማጣጣም በማስፈለጉ እንዲሁም ለሃገራዊ ልማት የሚያበረክተውን ሚና በብቃት ለመወጣት በሥነ-ልክና በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፎች የተደረሰበትን የሳይንስና ቴክኖሎጂ እድገት ደረጃ በመከተል በዘርፉ የጥናትና የምርምር ተግባራት፣ የካሊብሬሽን፣ የቴክኒክ አገልግሎቶች፣ የስልጠና እና የማማከር ስራዎችን ትኩረት አድርጎ እንዲሰራ በዓላማው ይህንን ታሳቢ በማድረግ ኢንስቲትዩቱ በማቋቋሚያ ደንብ የተሰጠውን ኃላፊነት እና ተግባር በአግባቡ ለመወጣትና በቀጣይ የታቀዱትን ተግባራት ለመፈጸም የሚያስችል አደረጃጀት ተጠንቶ በመጽደቁ በምደባ ሂደት ላይ ነው፡፡

የሰው ኃይል ግንባታን በተመለከተ ለ151 (ወ=134 እና ሴ=27) ሠራተኞች በተለያዩ ሙያዎች የአቅም ግንባታ ሥልጠና የተሰጠ ሲሆን የኦዲት ስራዎች በተመለከተ የ2015 በጀት ዓመት የፈሰስ ሂሳብ ሪፖርት ፣ የ4ኛ ሩብ ዓመት የሂሣብ ኦዲት ሪፖርት እና የ2016 በጀት ዓመት ከ1ኛ -3ኛ ሩብ ዓመት ሪፖርት በውስጥ ኦዲት አስተያየቶች ላይ የእርምት እርምጃ መወሰዱን ክትትል በማድረግ ሪፖርት ተዘጋጅቷል፡፡ የለውጥና መልካም አስተዳደር የአሰራር ስርዓቶች ከመዘርጋት አኳያ ተቋማዊ ለውጥ ላይ የማሻሻያ ሀሳብ ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡ በተጨማሪም ለተገልጋዮች የቅሬታ እና አቤቱታ ማስተናገጃ ስርአት ተግባራዊነቱ ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡

## 3. በቁልፍ የውጤት አመላካቾች ላይ የተመሰረተ የልማት ዕቅድ አፈጻጸም ትንተና

በአጠቃላይ የኢንስቲትዩቱ የ2016 በጀት ዓመት የዋና ዋና ተግባራት አፈጻጸም 86% ሲሆን በዝርዝር ሲታይ የተገልጋይ ዕይታ አፈጻጸም 86.9%፣ የፋይናንስ ዕይታ 92.5%፣ የውስጥ አሰራር ዕይታ 75% እና የመማርና እድገት እይታ 94% ነው፡፡

**ግብ 1፡ የደንበኛ /የባለድርሻ እርካታ ማሳደግ (ክንዉን 90%)፡፡**

**1.1 ጥናትና ምርምር ማካሄድ** (ክንውን 90%) ፡፡

**1.1.1 ሁለት ጥናትና ምርምር ፕሮፖዛል ለማጠናቀቅ ታቅዶ**

- የሙቀት መጠን መቆጣጠሪያ የምርምር ስራ ለመጀመር ፕሮፖዛል ተዘጋጅቶ ዲዛይኑ ተጠናቋል፡፡ ግብአት በአገር ውስጥ ገበያ መኖራቸውን የመለየት ስራ ተሰርቷል፡፡ የምርምር ስራውን ለመጀመር አሮጌው ላብራቶሪ በመፍረሱ እና አዲሱ ህንጻ ባለመጠናቀቁ አልተከናወነም፡፡

- የክትባት መድኃኒቶች ማቆያ ፍሪጅ ለማሻሻል ፕሮፖዛል እና ዲዛይን ተጠናቋል፡፡ ሆኖም አዲስ ኮምፔሬሰር በአገር ውስጥ ገበያ ባለመገኘቱ በቀጣይ በጀት ዓመት ከውጭ ሀገር ግዢ ለመፈጸም በዕቅድ ተይዟል (ክንውን 90%)፡፡

**1.2 የካሊብሬሽን አገልግሎቶች መስጠት** (ክንውን 80%) ፡፡

1.2.1 ለ31000 የካሊብሬሽን አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ በዋናው መ/ቤት 23784 እንዲሁም በቅርንጫፍ ላብራቶሮች 1070 በድምሩ 24854 የካሊብሬሽን አገልግሎት ተሰጥቷል (ክንውን 80%) ፡፡

## 1.3 የጥገና አገልግሎቶች መስጠት (ክንውን 84%)

1.3.1. ለ300 መሣሪያዎች የጥገና አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ254 መሳሪያዎች የጥገና አገልግሎት ተሰጥቷል (ክንውን 84.6%) ፡፡

## 1.4. የስልጠና አገልግሎቶች መስጠት (ክንውን 112.5%) ፡፡

1.4.1 በሥነ-ልክ እና በሳይንስ መሣሪያዎች ዘርፍ ለደንበኞች ሙያዊ ሥልጠና ለመስጠት ታቅዶ፡-

**በሥነ-ልክ ዘርፍ**

- ለኢትዮጵያ የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን ሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በነዳጅ ይዘት አለካክ እና በተቀባሪ የነዳጅ ማከማቻው አጠቃቀም እንዲሁም የነዳጅ ርክክብ፣ ጥራትና አያያዝ ላይ ለ13 (ወ=10,ሴ=3) ባለሙያዎች የጽንሰ ሀሳብና የተግባር ስልጠና ተሰጥቷቸዋል፤
- በአሜሪካው ፋርማኮፒያ ድጋፍ ለ8 (ወ=7, ሴ=1) የኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ባለሙያዎች በሙቀት ልኬትና በአለካክ ሥርዓት እርግጠኛ ያለ-መሆን መጠን መስላት ላይ የጽንሰ ሀሳብ ስልጠና ተሰቷቸዋል፡፡
- ከሱማሊላንድ የጥራት ቁጥጥር ኮሚሽን ለመጡ አንድ ወንድ የስነ-ልክ ባለሙያ በአስር የስልጠና ርዕሶች አጠቃላይ የስነ-ልክ ፅንሰ ሀሣብና ፋይዳው፣ በግዝፈት፣ ሚዛን፣ በይዘትና ዕፍጋት፣ ግፊት፣ በኃይልና ሃርድነስ፣ በሙቀትና በወበቅ ላይ የጽንሰ ሃሳብና የተግባር ስልጠናዎች ተሰጥቷል፡፡
- የኢትዮጵያ የኮንስትራክሽን ዲዛይንና ሱፐርቪዥን ሥራዎች ኮርፖሬሽን ምርምር ላቦራቶሪና ስልጠና ማዕከል ለመጡ ለ5 (ወ=2, ሴ=3) ባለሙያዎች በአራት የስልጠና ርዕሶች አጠቃላይ የስነ-ልክ ፅንሰ ሀሣብና ፣ በግዝፈት፣ ሚዛንና በይዘት ላይ የጽንሰ ሃሳብና የተግባር ስልጠናዎች ተሰቷቸዋል፡፡
- በአሜሪካው ፋርማኮፒያ ድጋፍ ለ50 (ወ=30, ሴ=20) ከተለያዩ ክልሎች ለተመረጡ የባዮሜዲካል መሐንዲሶች በCold chain equipment and General Metrology ላይ የጽንሰ ሀሳብ ስልጠና ተሰቷቸዋል፡፡

  በአጠቃላይ ለ76 (ወ=49,ሴ=27) ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

**በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፍ**

- ከአራት የግል ኩባንያዎች፣ ከፊስቱላ ሆስፒታል እና ከኢሥኢ ለተውጣጡ 13 ባለሙያዎች (ወ=10,ሴ=3) ሁለት የሥልጠና ኮርሶች በተከታታይ ተሰጥተዋል፡፡
- ከአዲስ አበባ ጤና ቢሮ ለተውጣጡ 14 ባለሙያዎች (ወ=9,ሴ=5) በሚከተሉት ሁለት የሥልጠና ኮርሶች በተከታታይ ተሰጥተዋል፡፡

1. Training course on Design, Implimentation and Troubleshooting Tequeniqus, Analogue electronics
2. Training course on Design, Implimentation and Troubleshooting Tequeniqus, Degital electronics **(ክንውን 112%)።**

## 1.5 የምክር አገልግሎቶች መስጠት (ክንውን 100%)

1.5.1 በሥነ-ልክ ዘርፍ የምክር አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ

**በሥነ-ልክ ዘርፍ**

ለኢትዮጵያ የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን በነዳጅ ይዘት አለካክ እና በተቀባሪ የነዳጅ ማከማቻው አጠቃቀም ላይ የምክር አገልግሎት ተሰቷቸዋል።

- ለ ODO International Export ድርጅት ካሊብሬት ሊደረጉ የሚችሉ የመለኪያ መሳሪያዎችን መለየት እንዲችሉ የምክር አገልግሎት ተሰጥቷቸዋል።

**በሳይንስ መሣሪያዎች ዘርፍ**

- ለኦሮሚያ ግብርና ግብዓቶች ቁጥጥር ባለሥልጣን የላቦራቶሪ መሳሪያዎች የኢንስፔክሽን አገልግሎት በመስጠት ሪፖርት ተዘጋጅቶ ተልኳል።
- ለኦሮሚያ ግብርና ግብዓቶች ቁጥጥር ባለሥልጣን የእርጥበት ማድረቂያ መሳሪያ የኢንስፔክሽን አገልግሎት በመስጠት ሪፖርት ተዘጋጅቶ ተልኳል።
- ለኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የሶላር ፓናል ሲስተም ስራ የቴክኒክ አገልግሎት በመስጠት ሪፖርት ተዘጋጅቶ ተልኳል (ክንውን 100%)።

## 1.6 የብቃት ማረጋገጥ አገልግሎቶች መስጠት (ክንውን 100%)

**1.6.1.** ለህክምና መሳሪያዎች ተከላ፣ ጥገናና ኮሚሽኒንግ የብቃት ማረጋገጥ አገልግሎቶች ለጠየቁ ደንበኞች 100% ለመስጠት ታቅዶ አገልግሎቱን ለጠየቁ 18 ደንበኞች የብቃት ማረጋገጫ ተሰጥቷል (ክንውን 100%)።

## 1.7 የተጠቃሚ እርካታ ጥናት ማድረግ (ክንውን 100%)።

1.7.1. የተገልጋይ እርካታ ለመመዘን ታቅዶ የተገልጋይ እርካታ ጥናት ሰነድ ተዘጋጅቶ በስራ አመራር ተመዝኗል (ክንውን 100%)።

**ግብ 2፡ ተደራሽነትን ማሳደግ** (ክንውን 75%)

2.1. በቅርንጫፍ ካሊብሬሽን ላብራቶሪዎች የአገልግሎት ወሰን ማስፋትና **ማ**ስቀጠል (ክንውን 50%) ፡፡

2.1.1. በጅማ ቅርንጫፍ ካሊብሬሽን ላብራቶሪዎች በሙቀት አለካክ መስክ የአገልግሎት ወሰን ለማስፋት የላብራቶሪ መሳሪያ ግዢ ለማጠናቀቅ ታቅዶ የላቦራቶሪ መሳሪያዎች ለመግዛት የበጀት ችግር በማጋጠሙ ለ2017 በጀት ዓመት በካፒታል በጀት ጠይቀን በፕላን ኮሚሽን እና በገንዘብ ሚ/ር ተቀባይነት በማግኘቱ አዳዲስ መሳሪያዎችን ለመግዛት የማነፃፀሪያ መሳሪያዎችን ዝርዝር ባህሪያት የተዘጋጀ ሲሆን በቀጣይ በጀት ዓመት የውጭ ሀገር ግዥዎችን ለመፈፀም ዝግጅቱ ተጠናቋል (ክንውን 50%) ፡፡

**2.2 የቴክኒክ ድጋፍ አገልግሎቶች መስጠት (ክንውን 100%)**

2.2.1 የጥገና ወርክሾኘ እና የካሊብሬሽን ላቦራቶር ለማቋቋም ጥያቄ ለሚያቀርብ የግል ባለሀብት፣ አምራችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የቴክኒክ ድጋፍ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ

**በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፍ**

1ኛ. ለእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት የላቦራቶሪ መሳሪያዎች ጥገና ወርክሾፐ የሚሆኑ አስፈላጊ የሆኑ የጥገናና የመለኪያ መሳሪያዎች ዝርዝር ስፔስፊኬሽን ተዘጋጅቷል፡፡

2ኛ. በጤና ሚ/ር ውስጥ ለሚገኙ ሆስፒታሎች የህክምና መሳሪያዎች ያሉበት ሁኔታ ላይ ዳሰሳና ፐርፎርማንስ ቴስት ሰራዎች ላይ በመሳተፍ የቴክኒክ ድጋፍ ተደርጓል ፡፡

**በሥነልክ ዘርፍ**

- በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ለህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የካሊብሬሽን ላቦራቶር ለማቋቋም እንዲችሉ የመሳሪያዎች ዝርዝር ባህሪ ጥናት በማድረግ አስፈላጊ ለሆኑት የመለኪያ መሳሪያዎች ግዢ ዝርዝር መስፈርት/Specification/ ተዘጋጅቷል፡፡
- ለኦሮሚያ ምርጥ ዘር ኢንተርፕራይዝ ቀደም ሲል በተዘጋጀላቸው የመለኪያ መሳሪያዎች ግዢ ዝርዝር መስፈርት /Specification/ መሰረት ስለመቅረባቸው በአቅራቢዎች የቀረቡ መለኪያ መሳሪያዎች በዕይታ ማረጋገጥ/Inspection/ ስራ ሁለት ጊዜ ተከናውኖላቸዋል (ክንውን 100%) ፡፡

**2.3 የኢንስቲትዩቱን ዌብሳይት ለንብኚዎች ምቹ እንዲሆን ማድረግ** (ክንውን 91.5%)

2.3.1. ኢንስቲትዩቱን በሚመለከት ለድረ-ገጽ የሚመጥኑ መረጃዎችን፣ ለማዘጋጀት፣ ለመጫንና ወቅታዊ እንዲሆኑ ለማድረግ ታቅዶ አዲስ እየለማ ባለው ድረ ገጽ ላይ በሙከራ ደረጃ መረጃዎችን የመጫን ሥራ ተሰርቷል (ክንውን 100%)፡፡

2.3.2. የMet/Team ሲስተምን ተግባራዊ በማድረግ የካሊብሬሽን ደንበኞችን የመረጃ አያያዝ አውቶሜት በማድረግ ከደንበኞች አገልግሎት እስከ ፈጻሚዎች ያለውን የመረጃ ልውውጥ ማዘመንና ደንበኞች ባሉበት ሁነው ስራቸው የት እንደደረሰ ክትትል የሚያደርጉበት ሲስተም ተግባራዊ ለማድረግ ታቅዶ

- የካሊብሬሽን ሲስተም አውቶሜት ለማድረግ ከኢንዱስሪያል ዳይሬክቶሬት ጋር ሜት ቲምን በከፊል ተግባራዊ የማድረግ ስራ ተጀምሯል፡፡ በተዋረድ ላሉ የደንበኞች አገልግሎት ሁሉም ባለሙያዎች እና ቡድን መሪዎች አካውንት ተከፍቶላቸው የስራ ላይ ስልጠና እንዲያደርጉ ሲስተሙ የተመቻቸ በመሆኑ

  በአፈጻጸም ሂደት ተግዳሮት የሆኑ ጉዳዮችን የመለየት ስራ እየተሰራ ነው (ክንውን 100%) ፡፡

**2.4. የግንዛቤ ማስጨበጫ መስጠት** (ክንውን 66.6%) ፡፡

2.4.1 በተመረጡ 3 አካባቢዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ለመስጠት ታቅዶ ኢንስቲትዩታችን ባሉት ቅርንጫፎች ሥር ለሚገኙ ደንበኞችና ባለድርሻ አካላት ከአራቱም የጥራት መሰረት ልማት ተቋማት ጋር በጥምረት በመሆን በጅማ እና በድሬዳዋ ከተማ ቅ/ጽ/ቤት ስር ለሚገኙ ደንበኞችና ባለድርሻ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ የተካሄደ ሲሆን ሦስተኛውን ዙር ለማድረግ የታቀደ ቢሆንም በበጀት እጥረት ምክንያት አልተከናወነም (ክንውን 66.6%) ፡፡

**ግብ 3 የበጀት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ** (ክንውን 94%) ፡፡

## 3.1. የፕሮግራም በጀት ዕቅድ ማዘጋጀት እና የበጀት አጠቃቀም መከታተል (ክንውን 92%)

3.1.1. የጸደቀውን በጀት በዕቅዱ መሰረት 100% ለመጠቀም ታቅዶ የ2016 በጀት ዓመት አፈጻጸም ተጨማሪ የተፈቀደልንን በጀት ጨምሮ 94% ሆኗል፡፡

## 3.2. የአገልግሎት ክፍያዎችና ተሰብሳቢ ሂሳቦች በወቅቱ ለመንግስት ገቢ ማድረግ (ክንውን 95%)

13 ሚሊዮን ብር የአገልግሎት ክፍያዎችና ሌሎች ገቢዎችን በመሰብሰብ በወቅቱ ለመንግስት ገቢ ለማድረግ ታቅዶ እስከ ሰኔ 14 ቀን 2016 ዓ.ም ብር 13,000,000 ተሰብስቧል (ክንውን 95%)፡፡

**3.3. የፋይናንስ ኦዲት ማከናወንና መከታተል** (ክንውን 100%)፡፡

3.3.1. የ2015 በጀት ዓመት የፈሰስ ሂሳብ ሪፖርትና የ4ኛ ሩብ ዓመት፣ የ2016 በጀት ዓመት የ1ኛ ፣ የ2ኛ እና 3ኛ ሩብ ዓመታት የሂሣብ ኦዲት ሪፖርት አዘጋጅቶ ለማቅረብ ታቅዶ በዕቅዱ

መሰረት የሂሳብ ሪፖርት ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ተደርጓል (ክንውን 100%) ::

**ግበ 4. የፋይናንስ ምንጮችን ማበራከት** (ክንውን 100%)

4.1.1 የድጋፍ ፕሮጀክት ሰነድ (ፕሮፖዛል) ማዘጋጀት ፣ ማጸደቅ እና ድጋፍ ሰጭ ድርጅቶችን ለማፈላለግ ታቅዶ TMEA (Trade mark east Africa) በተወሰኑ የmetrology ዘርፎች የአቅም ግንባታ እንዲሆን Proposal ተቀርፆ ተልኳል እንዲሁም የካሊብሬሽን አልግሎቶች ወሰን ማጐልበቻ የላቦራቶሪ መሳሪያዎች እና የሞባይል ላቦራቶሪዎች ግዥ ጥናት ፕሮጀክት ለ2017 በጀት ዓመት የበጀት ጥያቄ ለገ/ሚ ተልኳል (ክንውን 100%)፡፡

**ግብ 5 አለም አቀፍ ተቀባይነት ማሳደግ** (ክንውን 60.8%)

**5.1. ዓለም ዓቀፍ እርከን ተዋረድ ትስስር መጠበቅና ማሰራጨት** (ክንውን 110%)

5.1.1. በግዝፈት፣ በሙቀት፣ በዳይሜንሽናል፣ በጊዜና ድግግሞሽ እና በግፊት አለካክ መስኮች ብሔራዊ የመጀመሪያ ደረጃ የማነፃፀሪያ መለኪያ መሣሪያዎችን ዓለም አቀፍ የዕርከን ተዋረድ ትስስር ለመጠበቅ ታቅዶ፡-

- ✓ በጀርመን የስነ-ልክ ኢንስቲትዩት ኢትዮጵያ ካለው ፕሮጀክት ድጋፍ የዳይሜንሽናል እና የግፊት ብሔራዊ የመጀመሪያ ደረጃ የማነጻጸሪያ መለኪያ መሳሪያዎች የዕርከን ተዋረድ ትስስር ማስጠበቅ ተችሏል፡፡
- ✓ በግዝፈት፣ በሙቀት፣ በሚዛን፣ በኃይል፣ በዳይሜንሽናል፣ በጊዜና ድግግሞሽ የመጀመሪያ ደረጃ ብሔራዊ የማነጻጸሪያ ስታንዳርዶች በደቡብ አፍሪካ የሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት የዕርከን ተዋረድ ትስስር ማስጠበቅ ተችሏል (ክንውን 110%)፡፡

5.1.2. ለ232 በዋናው መስሪያ ቤት እና በደንበኞች የካሊብሬሽን ላቦራቶሮች ለሚገኙ ሁለተኛ ምድብ ማነጻጸሪያ መለኪያ መሳሪያዎች ዓለም አቀፍ የዕርከን ተዋረድ ትስስር ለማሰራጨት ታቅዶ በግዝፈት 75 ፣በሙቀት 70፣በኤሌክትሪካል 25፣ በዳይሜንሽናል 97፣ በግፊት 23 እና በአጠቃላይ 290 መሳሪያዎች ዓለም አቀፍ እርከን ተዋረድ ትስስር ተሰራጭቷል (ክንውን 125%) ፡፡

**5.2. ዓለም አቀፍ እውቅና የተገኘባቸው የአለካክ መስኮች/ወሰን ማስቀጠል (ክንውን 30%)**

**5.2.1** በላቦራቶሮች ህንጻ ለውጥ ምክንያት ዓለም አቀፍ ዕውቅናቸው በፈቃደኝነት የታገዱት የውስጥ ላቦራቶር (የግዝፈት፣ የኤሌክትሪካል፣ የሙቀት፣ የግፊትና የይዘት) የአለካክ መስኮች እንደገና ዓለም አቀፍ ዕውቅና ለማግኘት ማደራጀትና ዝግጁ ለማድረግ ታቅዶ የላቦራቶሮች ህንጻ ሰላልተጠናቀቀ ስራው አልተሰራም (ክንውን 0%)፡፡

5.2.2 ዓለም አቀፍ ዕዉቅና በነበራቸዉ የውስጥ ካሊብሬሽን (የግዝፈት፣ በኤሌክትሪካል፣ በሙቀት፣ ግፊትና በይዘት (5)፣ በተንቀሳቃሽ (4) እና በመስክ (2) የካሊብሬሽን የአለካክ መስኮች ዓመታዊ የውስጥ የጥራት ኦዲት ለማከናወን ታቅዶ የላቦራቶሮች ህንጻ ሰላልተጠናቀቀ ስራው አልተሰራም (ክንውን 0%)፡፡

5.2.5 ሀዋሳ ቅርንጫፍ ላቦራቶሪዎች ዕውቅና ባልተገኘበት በሚዛን ካሊብሬሽን አገልግሎት በውስጥ ባለሙያ ኢንተርናሽናል አክሪዲቴሽን ለማግኘት ታቅዶ በሀዋሳ ቅርንጫፍ ላቦራቶሪዎች ዕውቅና ባልተገኘበት በሚዛን ካሊብሬሽን አገልግሎት በውስጥ ባለሙያ ኢንተርናሽናል አክሪዲቴሽን ተገኝቷል (ክንውን 100%)፡፡

5.3. በአዳዲስ የአለካክ መስኮች/ወሰን እውቅናን ማስፋት (ክንውኑ 30%)፡፡

5.3.1 በወበቅ (Humidity)፣ በእርጥበት (Mositure) እና በኃይል (Force) የአለካክ መስኮች የካሊብሬሽን የአሰራር ስርዓት ሰነድ ማዘጋጀት እና ዕውቅና ለማስፋት ታቅዶ በወበቅ፣ በሀይልና በእርጥበት የአለካክ መስኮች የአሠራር ሥርዓት ሰነድ ተዘጋጅቷል እውቅና ለማሰጠት በኢትዮጵያ የአክሪዲቴሽን አገልግሎት ጥያቄ ቀርቧል (ክንውኑ 75%) ፡፡

5.3.2 በዳይሜንሽናል አለካክ መስክ ዓለም አቀፍ ዕውቅና ለማግኘት ስልጠናዎች ማግኘትና የካሊብሬሽን የአሰራር መመሪያዎች /Procedures/ ለመከለስ ታቅዶ አልተከናወነም (ክንውኑ 0%) ፡፡ ያልተከናወነበት ምክንያት የአዲሱ ህንጻ ላቦራቶሮች ግንባታ ባለመጠናቀቁ ወደ ተግባር መግባት ባለመቻሉ ነው፡፡

5.4 በዓለም አቀፍ የሥነ-ልክ ድርጅት መረጃ ቋት BIPM-KCDB) ማስመዝገብ (ክንውን 67.3%)፡፡

5.4.1 የሙቀት እና የይዘት የካሊብሬሽን ልኬት ብቃት/CMC/ በዓለም አቀፍ የሥነ-ልክ ድርጅት መረጃ ቋት /BIPM-KCDB/ እንዲመዘገብ ክትትል ለማድረግ ታቅዶ በዓለም ዓቀፍ የሥነ-ልክ ድርጅት መረጃ ቋት /BIPM-KCDB/ ለማስመዝገብ በተላከው የካሊብሬሽን ልኬት ብቃት/CMC/፣ በተለያዩ RMO በተሰጠው አስተያየት መሰረት CMC በመከለስ በሙቀት አለካክ መስክ በ4 የልኬት ባህያት ማስመዝገብ ተችሏል፡፡ በይዘት አለካክ መስክ የተጠየቀው ተሟልቶ ውጤት በመጠባበቅ ላይ ነን (ክንውን 87%)፡፡

5.4.2 ዓለም አቀፍ ዕውቅና ያላቸው የአለካክ መሰኮች የካሊብሬሽን ልኬት ብቃታቸውን /CMC/ በዓለም አቀፍ የሥነ-ልክ ድርጅት መረጃ ቋት /BIPM-KCDB/ ለማስመዝገብ በሂደት ላይ ያሉ እና አዳዲስ የላቦራቶሮች ቁልፍና ድጋፍ ንጽጽር ፕሮግራሞች መከታተልና ለመሳተፍ ታቅዶ፡-

- በሙቀት ስነ-ልክ Comparison of the calibration of noble metal thermocouple from 0 ºC up to 1100 ºC ዘርፍ AFRIMETS.T-S7 ላይ የንጽጽር ፕሮግራም ተደርገዋል

- **በወበቅ ስነ-ልክ** multilateral comparison measurement on the calibration of climatic chambers according to DKD-R 5-7 **ላይ የንጽጽር ፕሮግራም ተደርገዋል** (ክንውን 40%)፡፡

5.4.3 በተገመገመው የጥራት ሥራ አመራር አሰራር ሥርዓት ሰነድ መሰረት ብቁ የርስበርስ ንጽጽር ውጤት ያላቸው የአለካክ መስኮች /ኤሌክትሪካል/ በዓለም አቀፍ የሥነ-ልክ ድርጅት መረጃ ቋት /BIPM-KCDB/ የካሊብሬሽን ልኬት ብቃት/CMC/ ለማስመዝገብ ማመልከቻ ለማቅረብ ታቅዶ የመጀመሪያው ድራፍት A ላይ በተሰጠው አስተያየት መሰረት ፓይለት ላብራቶሩ አስተያየቶችን አካቶ የካሊብሬሽን ልኬት ብቃት/CMC/ ምዝገባ ጥያቄ ለማቅረብ የመጨረሻው ሪፖርት እየተጠበቀ ነው (ክንውን 75%)

**5.5 ከአህጉራዊና ዓለምአቀፍ የሥነልክ ተቋማት ጋር ተሳትፎ ማድረግ** (ክንውን 100%)

**5.5.1** በአህጉራዊ AFRIMET እና NEWMET ዓመታዊ የቴክኒካል ስብሰባዎች ላይ መሳተፍ እና የንጽጽር ፕሮግራሞችን ለማመቻቸት ታቅዶ በአህጉራዊ AFRIMET እና NEWMET ዓመታዊ የቴክኒካል ስብሰባዎች ላይ ለመሳተፍ እና የንጽጽር ፕሮግራሞችን ለማመቻቸት July 17 online ለመሳተፍ ተጠናቋል (ክንውን 100%)

**5.6 የጥራት ስራ አመራር ስርዓቶችን በመለየት ተግባራዊ ማድረግ** (ክንውን 50%)

**5.6.1 ( ISO 9001:2015) ተግባራዊ ለማድረግ ለስራ አመራር አባላት እና ለሚመለከታቸው** ባለሙያዎች በኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ (ISO 9001:2015) ተግባራዊ ለማድረግ ለስራ አመራር አባላት እና ለሚመለከታቸው ባለሙያዎች በኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት ስልጠና እንዲያገኙ ጥያቄ ቀርቧል (ክንውን 50%)፡፡ አፈጻጸሙ ዝቅ ያለበት ምክንያት የህንጻ ግንባታ ክትትል ስራዎች፣ በጥራት መሰረተ ልማት ፕሮጀክት የተገዙ መሳሪያዎች ወደ ስራ የማስገባት ጥረቶች እና የኢንስቲትዩቱን አደረጃጀት የማጸደቅ ስራዎች ትኩረት ሰጥቶ መስራት በማስፈለጉ እና የተያዘውን የስራ አመራር ስርዓት ለመተግበር የግዜ እጥረት በማጋጠሙ ነው፡፡

**ግብ 6. የአለካክ ወሰኖችን ማሳደግ** (ክንውን 83.3%)

**6.1. የአለካክ መስክ/ወሰን ማሳደግ** (ክንውን 83.3%)

6.1.1 በግዝፈት የአለካክ መስክ የልኬት ትክክለኝነት አሁን ካለበት ከ E2 ወደ E1/E0 ደረጃ ለማሳደግ ስልጠናዎችን በመውሰድ ቅደመ ዝግጅት ለማጠናቀቅ ታቅዶ በግዝፈት የአለካክ መስክ የልኬት ትክክለኝነት አሁን ካለበት ከ E2 ወደ E1/E0 ደረጃ ለማሳደግ ስልጠና መውሰድ ባይቻልም በራስ

ጥረት የአሰራር ስርዓት (ፕሮሲጀር)ተሰርተዋል፡፡ የማሻሻያ ስልጠና ማግኘት ይቀራል (ክንውን 100%)

6.1.2. በኬሚካል ሥነ-ልክ፣ በፎቶሜትሪና ራዲዮሜትሪ እንዲሁም በጊዜና ድግግሞሽ የአለካክ መስኮች በስፔክትሮፎቶ ሜትር አለካክ መስክ የካሊብሬሽን አገልግሎት ለማስጀመር የሚያስችል ስልጠናዎችን በማግኘት ላቦራቶሮችን ለማደራጀት ታቅዶ፡-

- በኬሚካል ሥነ-ልክ በreferance material production method ISO 17034:2016 ላይ ከ(NMISA)በመጣች ባለሙያ ለ4 ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል፣ በባዮ ኢመርጅንግ ኢንስቲትዩት በተዘጋጀዉ የማይክሮ ባዮሎጂ የኬሚካል ዳይሉሽን ሜተድ ስልጠና ላይ ተሳትፎ ተደርጓል፡
- በፎቶሜትሪና ራዲዮሜትሪ Hitachi U_3900H spectrophotometer በሚል መሳርያ ላይ በዶክተር ፍራንዝ ለአራት (4) ባለሞያዎች ለ3 ወር ያህል ስልጠና ተሰጥቷል::
- በጊዜና ድግግሞሽ የአለካክ መስክ የታሰበው ስልጠና የወርልድ ባንክ ግዥ ይከናወናል በሚል ታሳቢ ስለነበር አልተከናወነም ነገር ግን centrifuge calibration በውስጥ ባለሙያ ስልጠና በመስጠት ስራ ተጀምሯል (ክንውን 100%)፡፡

**ግብ 7 አሰራር ቅልጥፍናን ማሻሻል** (ክንውን 97%)

**7.1 የተሻሻሉና አዳዲስ ኦላይን ሲስተሞች ተግባራዊ ማድረግ** (ክንውን 95%)

**7.1.1** የሳይንስ መሳሪያዎች የብቃት ማረጋገጫ አገልግሎትን አውቶሜት በማድረግ ተጠቃሚዎች ባሉበት ሆነው ማመልከት እንዲችሉ እንዲሁም ክትትል ማድረግ የሚያስችል አገልግሎትን ለማስጀመር ታቅዶ በአለም ባንክ ድጋፍ በመሰራት ላይ ያሉ የሳይንስ መሳሪያዎችን የሰርተፊኬሽን አገልግሎትን ለማዘመን የሚያስችለውን ሲስተም ስራው ተጠናቋል ፡፡ የደህንነት ማረጋገጥ ስራዎች በኢንሳ እንዲከናወኑ ከአልሚው እና ከፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ጋር ከስምምነት ተደርሷል (ክንውን 90%) ፡፡

7.1.2. በተቋሙ ተግባራዊ የተደረጉ የደንበኞች አገልግሎት ሲስተሞችን ተፈጻሚነት ለማዝለቅ ድጋፍና ክትትል ለማድረግ ታቅዶ በአለም ባንክ ድጋፍ እየተሰሩ ያሉ የተለያዩ ሲስተሞችን ተግባራዊ ለማድረግ ከተጠቃሚዎች እና ከአልሚ ድርጅቱ ጋር በጋራ በመሆን ሲስተሞችን ማለትም ከዌብፖርታል ጋር እየተለሙ የሚገኙ የጥገና የአገልግሎት መጠየቂያ፣ የደንበኞች ቅሬታ ማስተናገጃ ሲስተሞችን እና የውስጥ አገልግሎት መጠየቂያ ሲስተሞችን በማስገባት ሂደት በየሲሰተሞቹ ላይ የቀሩ ስራዎች እንዲስተካከሉ ለአልሚ ድርጅቱ የመጨረሻ አስተያየት ተልኮ በዚህ ወር እንደሚያስረክብ ተነጋግረን አልሚውን በመጠባበቅ ላይ እንገኛለን (ክንውን 100%)፡፡

**7.2 የህግ ክትትልና ድጋፍ አግልግሎት መስጠት (ክንውን 100%)**

7.2.1 በኢንስቲትዩቱ የሚቀርቡ የፍትሐብሄር ጉዳዮችን ማቅረብ፣ መከራከር መከታተልና የኢንስቲትዩቱን ጥቅም በህግ አግባብ ለማስጠበቅ ታቅዶ በመደበኛ ፍርድ ቤት በከሳሽነት በተከሳሽነት በጣልቃገብ፤ በይግባኝ እና በአፈጻጸም የቀረቡ ጉዳዮች ክርክር ተደርጎባቸው፤ ሁሉም ውሳኔ አግኝተዋል (ክንውን 100%) ፡፡

7.2.2 ተዘጋጅተው የሚቀርቡ ረቂቅ የህግ ማእቀፎችን ቅርጽና ይዘት ማስጠበቅና አስፈላጊውን ክትትል ለማድረግ ታቅዶ በበጀት ዓመቱ አዲስ ተዘጋጅቶ የቀረበ የህግ ማእቀፍ የለም ነገር ግን በ2015 በጀት የተሰሩና ለ2016 በጀት የተላለፉ የህግ ማእቀፎች

1ኛ. ረቂቅ ደንብ በሚንስቴር መስሪያ ቤቱ ክትትል ውስጥ ሲሆን፤

2ኛ. የትምህርትና ስልጠና የውስጥ አፈጻጸም መመሪያ ተጠናቆ ለበላይ ሃላፊ ለአስተያየት ቀርቧል (ክንውን 100%) ፡፡

7.2.3 የኢንስቲትዩቱን የክፍያ ሰነድ እንዲጸድቅ ለሚመለከተው አካል ለማቅረብ ታቅዶ የክፍያ ሰነድ ተዘጋጅቶ እንዲጸድቅ ለሚመለከተው አካል ቀርቧል (ክንውን 100%)፡፡

**7.3 የአገልግሎት ፣የመሳሪያ ግዢ እና የአባልነት ክፍያ መፈጸም** (ክንውን 95%)

7.3.1. በግዥ ዕቅዱ መሠረት የሀገር ውስጥ እና የውጪ ግዥ ለመፈፀም ታቅዶ በዓመታዊ የግዥ እቅድ መሠረት በEGP ብሔራዊ ጨረታ የግዥ ዘዴ ፋየር ዌል፣ የኮምፒውተር ጥገና፣ የጥበቃ እና የፅዳት አገልግሎት፣ የሆቴል አገልግሎት ግዥ፣ የሠራተኞች የደንብ ልብስ፣ላፕቶፕ ኮምፒውተሮች፣ስፒከር፣በ EGP ሲስተም በዋጋ ማቅረቢያ ዘዴ፣ የፅሕፈት መሳሪያ፣ የተለያዩ የተሽከርካሪ ጐማ፣ ባትሪ እና የሆቴል አገልግሎት ግዥዎች የተፈፀመ ሲሆን በማዕቀፍ ስምምነት የሚፈፀሙ ግዥዎች መካከል የፅህፈት መሳሪያ/ወረቀት እና እስክርቢቶ፣ የፅዳት እቃዎች /ሶፍት፣ የልብስ ሳሙና ፣ የእጅ ሳሙና፣ፈሳሽ ሳሙና እና ኦሞ/ ተገዝቷል፡፡ የሳይንስ መሳሪያዎች፣ የሜትሮሎጂ እቃዎች እና የጋራዥ አገልግሎት በተደጋጋሚ ጨረታ በሲስተም አውጥተን ተወዳዳሪ ባለመቅረቡ ግዢ መፈጸም አልተቻለም (ክንውን 95%)፡፡

**7.4 የንብረት ቆጠራ ማካሄድ እና ስራ ላይ የማይውሉ ንብረቶችን በወቅቱ ማስወገድ** (ክንውን 80%)፡፡

7.4.1 በዓመታዊ ንብረት ቆጠራ ውጤት መሠረት ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ ንብረቶችን በየዓይነታቸው መለየት እና በአስወጋጅ ኮሚቴ እንዲወገዱ ለማድረግ ታቅዶ ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ተጠናቆ ሪፖርት ቀርቧል የማስወገድ ስራ ይቀራል (ክንውን 80%) ፡፡

**ግብ 8 ቅንጅታዊ አሰራር ማሻሻል** (ክንውን 25%) ፡፡

8.1.1 ከተለያዩ ዩኒቨርስቲዎችና የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጆች ለሚመጡ ተማሪዎች ኢንተርንሺፕ ፕሮግራም ለማካሄድ ታቅዶ አልተከናወነም (ክንውን 0%)፡፡ ያተከናወነበት ምክንያት ዩኒቨርስቲዎቹ ተማሪዎች ያላኩ በመሆኑ ነው፡፡

**8.2. ከአቻ የውጪ የሥነ-ልክ ተቋማት ጋር በትብብር መስራት** (ክንውን 100%) ፡፡

8.2.1 ከጀርመን (PTB)፣ከደቡብ ኮርያ (KRISS)፣ከደቡብ አፍሪካ (NMISa)፣ ከቱርክ (UME)፣ ከሶማሌላንድ (SQCC) ሥነ-ልክ ተቋማት ጋር አብሮ መስራት የሚያስችሉ የአሰራር ዘዴዎች በማጥናት ተግባራዊ ለማድረግ ታቅዶ ከደቡብ አፍሪካ የስነ-ልክ ኢንስቲትዩት ጋር በጋራ ለመስራት የሚያስችል የስምምነት ሰነድ ፊርማ ተከናውኗል፡፡ ከ PTB እና ከ SQCC ጋር በቅንጅት በርካታ ስራዎችን ማከናወን ተችሏል (ክንውን 100%) ፡፡

**8.3. ከጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት ጋር በትብብር መስራት** (ክንውን 100%) ፡፡

8.3.1 ከጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት ጋር በትብብር ለመስራት ታቅዶ ከአራቱ የጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት ጋር በመተባበር የጋራ የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራም በማዘጋጀት ለደንበኞች ግንዛቤ ተሰጥቷል (ክንውን 100%) ፡፡

**ግብ 9 የሰራተኛውን ብቃት ማሳደግ** (ክንውን 91%) ፡፡

**9.1 የሰው ሀብት ልማት ማልማት** (ክንውን 93.8%) ፡፡

9.1.1. ለ 200 ሠራተኞች ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ

- በEGP እና Attendance ለ21 (ወንድ= 13, ሴት= 8) ባለሙያዎች
- ለፀሐፊዎች ሚስጥራዊ የፋይል አያያዝ፣የቢሮ ማሽኖችን አያያዝና አጠቃቀም እና የቢሮ የስነ-ምግባር መርሆች ዙሪያ 11(ወንድ=3, ሴት=8)

- በትራንስፖርት የስምሪትና የነዳጅ አጠቃቀም መመሪያ ላይ ለ5 ቀን 22(ወንድ=18, ሴት=4) ባለሙያዎች
- በክፍያ ስርዓት በደንበኞች አገልግሎት አሰጣጣ በሰራተኞች ድልድል መመሪያ እና በአንድ ጊዜ ድልድል መመሪያ ዙሪየ ለ7 ቀን 42(ወንድ=34, ሴት=8) ባለሙያዎች
- የአመራር የስልጠና ርዕስ ላይ በጤና አደም የስልጠናና ሰራተኞች 2 ቀን 8(ወንድ=7, ሴት=1) ባለሙያዎች
- ለ8 ቀን ለ44 (ወንድ=36,ሴት= 8) ኃላፊዎችና ሠራተኞ እንዲሁም ለ3 ወንድ ሹፌሮች የአውቶ መካኒክ ስልጠና ለ10 ቀን ተሰጥቷል፡፡

በአጠቃላይ 151 (ወንድ=114, ሴት= 37) አመራሮችና ሰራተኞች ስልጠና ተሰጥቷል (ክንውን 75%) ፡፡

9.1.2 ለ2 ሠራተኞች ሁለተኛ እና ሶስተኛ ዲግሪ የትምህርት ዕድል ለመስጠት ታቅዶ ለሁለት ሰራተኛ የትምህርት ዕድል ተሰጥቷል (ክንውን 100%)፡፡

**9.2. የሴቶችን ተሳትፎ ለማሳደግ ስልቶችን መቀየስ፣ መከታተልና ማጠናከር** (ክንውን 92%)፡፡

9.2.1 ኤች አይቪ በደማቸዉ ዉስጥ ለሚገኝ ሠራተኞችና ወላጆቻቸዉን ላጡ ሕፃናት ብር 21600 ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ 19,495.7 ብር ድጋፍ ተደርጓል (ክንውን 90.25%)፡፡

**9.2.2** የስርዓተ ጾታ ጋድላይን አፈጻጸም ተግባራዊነት ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል (ክንውን 100%)፡፡ በተጨማሪም በሴቶች ፎረም ምስረታ ላይ ግንዛቤ በመፍጠር 7 አባላቶች ተመርጠዋል (ክንውን 100%)፡፡

**9.3. የተቀናጀ የሙስናና የመከላከል ስትራቴጂ ተግባራዊ ማድረግ (ክንውን 100%) ፡፡**

9.3.1. በተቋም ለሙስና ተጋላጭነት ስጋት በሆኑ አሰራሮች ላይ የተደረገውን ጥናት ተግባራዊ ለማድረግ ታቅዶ በካሊብሬሽን ዙሪያ በተጠና ጥናት ላይ በስራ አመራርና በቡድን መሪዎች ተገምግሞ የአሰራር ማነዋል እንዲዘጋጅ አቅጣጫ ተቀምጧል፡፡ (ክንውን 100%) ፡፡

9.3.2 የተቋሙ የሥነ-ልክ ባለሙያዎች ሀብታቸውን እንዲያስመዘግቡ ለማድረግ ታቅዶ የተቋሙ የበላይ አመራሮች፣ ዳይሬክተሮች፣ ቡድን መሪዎችና የስነ-ልክ ባለሙያዎች ሀብታቸውን በሀርድ ኮፒ እንዲያስመዘግቡ ተደርጓል (ክንውን 100%) ፡፡

**ግብ 10. የስራ አካባቢና መሰረተ ልማት ማሻሻል** (ክንውን 100%) ፡፡

**10.1. የአካባቢ ብክለትንና በህብረተሰቡ ጤና ጉዳት መቀነስ** (ክንውን 100%) ፡፡

10.1.1 የሁለተኛ ምድብ የጨረራ ላቦራቶር/SSDL/ ጨረር ልቀት መቆጣጠርና በአከባቢው የሚያመነጨውን መጠን በየጊዜው በመከታተል ሪፖርት ለማቅረብ ታቅዶ የሁለተኛ ምድብ የጨረራ ላቦራቶር/SSDL/ ጨረር ልቀት መቆጣጠርና በአከባቢው የሚያመነጨውን መጠን በሳምንት አንድ ጊዜ የሰርቪሊያንስ ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡ (ከፍተኛ የተገኘ ልኬት 0.28 µG ) ሲሆን ከ ኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ አውቶሪቲ ጋር በመሆን ሰርቪልያንስ ስራ ተሰርቷል የተገኘ ውጤትም በር ተከፍቶ (4.96 µG, 680 µG East, 5.38 µG West, 3.10 µG North) ሲሆን ከክፍል ውጭ በአካባቢው ላይ ምንም ችግር የማይፈጥር መሆኑ ተረጋግጧል (ክንውን 100%) ፡፡

**10.2 ተስማሚ የሆኑ የሥራ ቦታዎች ማዘጋጀት** (ክንውን 100%) ፡፡

**10.2.1** የጠቅላላ አገልግሎት ስራ ተግባራዊ ለማድረግ ታቅዶ የግቢ ፅዳትና ውበት በወቅቱ ስለመሰራቱ ፣በውል የተቀጠሩ የጥበቃና የፅዳት ሰራተኞች ላይ ቁጥጥርና ክትትል እንዲሁም ተሽከርካሪዎች የጥገና ስራ ክትትል ተደርጓል ፡፡ የስልክ መስመርን በተመለከተ የኮቴቤ ጊቢ ስልክ ሙሉ በሙሉ የማይሰራ በመሆኑ ከቴሌኮሚኒኬሽን መ/ቤት ክትትል እየተደረገ ነው (ክንውን 100%) ፡፡

**10.3 የኢ/ኮ/ቴ መሠረተ ልማት ደህንነትና ወቅታዊነት ማስጠበቅ**

**10.3.1** የኢንስቲትዩቱን የኔትወርክ መሠረተ ልማት 24/7 ደህንነትና ወቅታዊነት ማስጠበቅ እና ለተጠቃሚዎች የቴክኒክ ድጋፍ ለመስጠት ታቅዶ ለኢንስቲትዩቱ የኔትወርክ መሰረተ ልማት ውስጥ ለሚፈጠሩ ለ13 አዳዲስ የኔትወርክ ገመድ ዝርጋታ ፤ 5 ነባር የኔትወርክ ኬብል የማስተካከል፤ በየእለቱ የሰርቨር ደህንነትን ማረጋገጥ ስራዎች ተሰርቷል (ክንውን 100%) ፡፡

**10.4 የለውጥና መልካም አስተዳደር የአሰራር ስርዓቶች መዘርጋት (ክንውን 100%) ፡፡**

10.4.1. ተቋማዊ ለውጥ ላይ የማሻሻያ ሀሳብ ዶክመንት ለማቅረብ ታቅዶ ተቋማዊ ለውጥ ላይ የማሻሻያ ሀሳብ ሰነድ ተዘጋጅቷል (ክንውን 100%) ፡፡

10.4.2 የውስጥ፣ የውጭ ቅሬታና አስተያየት በመቀበል እንዲፈቱ ለሚመለከተው በማቅረብና እርምጃ ለማስወሰድ ታቅዶ ከደንበኞች የሚነሱ ቅሬታዎች፡- ቀጠሮ በጣም ረጅም መሆኑ፣ ስታንዳርድ መሳሪያዎች ደረጃቸውን የጠበቁ አለመሆን፣ የአገልግሎት ክፍያ online አለመሆኑ እና የአገልግሎት ወሰን ውስን መሆኑ የሚል አስተያየት የቀረቡ ሲሆን እንዲፈቱ ለሚመለከተው አካል ቀርቧል (ክንውን 100%) ፡፡

10.4.3. የውስጥ ተገልጋይ እርካታ ለመመዘን ታቅዶ ምዘናው ተከናውኖ የእርካታው መጠን 75% ሆኗል (ክንውን 100%) ፡፡

**ግብ 11 የክትትልና የግምገማ ስርዓትን ማሻሻል** (ክንውን **100%**) ፡፡

**11.1 ፕሮጀክቶችን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ (ክንውን 100%) ፡፡**

11.1.1. ግንባታቸው ባለቀ ወይም በከፊል አልቀው ስራ እንዲጀምርባቸው የተወሰኑ ላብራቶሮችን ወርኪግ ቤንቾች እና ሌሎች አስፈላጊ ፋሲሊቲዎች የማሟላት ስራዎችን ለመከታተልና ለመደገፍ ታቅዶ አስፈላጊ ፋሲሊቲዎች በወቅቱ የማሟላትና ስራዎችን የመከታተልና የመደገፍ ስራ ተሰርቷል (ክንውን 100%)፡፡

**11.2 ውጤት ተኮር ዕቅድ ማዘጋጀትና አፈጻጸም መገምገም** (ክንውን 100%) ፡፡

**11.2.1** የውጤት ተኮር ዕቅድ ማዘጋጀትና በየደረጃው ለመፈራረም ታቅዶ የ2016 በጀት ዓመት ውጤት ተኮር ዕቅድ በየደረጃው በመፈራረም ካስኬድ ተደርጓል፡፡

የ2016 በጀት ዓመት የመጀመሪያው የ6 ወር ውጤት ተኮር ምዘና ተካሂዷል

- በጣም ከፍተኛ 82 (ወ=52, ሴ=30) ሠራተኞች
- ከፍተኛ 79 (ወ=40 ሴ=39) ሠራተኞች፤
- መካከለኛ 3(ወ=3, ሴ=0) ሠራተኞች፤ አፈፃፀም ያስመዘገቡ ሲሆን በአጠቃላይ 164 ሠራተኞች (ወ=95 ሴ=69) ምዘና ተጠናቋል፡፡

(ክንውን 100%) ፡፡

## 4. ዓበይት ተግባራት ጠንካራና ደካማ ጎን

**ጠንካራ ጐን**

- የሙቀት የካሊብሬሽን ልኬት ብቃት/CMC/ በዓለም አቀፍ የሥነ-ልክ ድርጅት መረጃ ቋት ማስመዝገብ መቻሉ
- የካሊብሬሽን ላቦራቶር እና የጥገና ወርክሾኘ ለማቋቋም ጥያቄ ለሚያቀርቡ የግል ባለሃብት፤ አምራችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የቴክኒክ ድጋፍ አገልግሎት መሰጠቱ፤
- በሀዋሳ ቅርንጫፍ ላቦራቶሪዎች ዕውቅና ባልተገኘበት በሚዛን ካሊብሬሽን አገልግሎቶች በውስጥ ባለሙያ አለም አቀፍ ዕውቅና መገኘቱ፤
- ግንባታቸው ባለቀ ወይም በከፊል አልቀው ስራ እንዲጀምርባቸው የተወሰኑ ላብራቶሮችን ወርኪግ ቤንቾች እና ሌሎች አስፈላጊ ፋሲሊቲዎች ለማሟላት ኮሚቴ ተዋቅሮ የክትትል ስራ መሰራቱ፤
- ከጀርመን (PTB)፣ከደቡብ ኮርያ (KRISS)፣ከደቡብ አፍሪካ (NMISa)፣ እና ከሶማሌላንድ (SQCC) ሥነ-ልክ ተቋማት ጋር አብሮ መስራት መቻሉ
- የተቋሙን አደረጃጀት በመከታተል ማጸደቅ መቻሉ፤

**ደካማ ጐን**

- ዓለም አቀፍ ዕዉቅና በነበራቸዉ የውስጥ ካሊብሬሽን የአለካክ መስኮች ዓመታዊ የውስጥ የጥራት ኦዲት ማከናወን አለመቻሉ
- የግንዛቤ ማስጨበጫ መስጠት አፈፃፀሙ ዝቅተኛ መሆኑ
- (ISO 9001:2015) ተግባራዊ ለማድረግ ለስራ አመራር አባላት እና ለሚመለከታቸው ባለሙያዎች በኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት ስልጠና መስጠት አለመቻሉ
- ኢንተርንሽፐ ፕሮግራም አለመከናወኑ

## 5. ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች

**ያጋጠሙ ችግሮች**

- የተሽከርካሪ እጥረት መኖሩ ፤
- በጥራት መሰረተ ልማት ፕሮጀክት እየተገነቡ ያሉ ህንጻዎች የግንባታ ሥራ እና በጥራት መሰረተ ልማት ፕሮጀክት እየተገዙ ያሉ ዕቃዎች የሚተከሉበት ግዜ አለመጣጣም፤

**የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች**

- ከን/ቀ/ት/ሚኒስቴር ጋር በመሆን የቅርብ ክትትል በማድረግ የህንጻው ስራ እንዲፋጠን ክትትል በመደረግ ላይ ይገኛል፤

## 6. የ2016 በጀት ዓመት የሰው ኃይል መረጃ ሪፖርት

| ተ.ቁ | የሠራተኞች የት/ደረጃ | በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ የነበሩ | | | በበጀት ዓመቱ አዲስ የተቀጠሩ | | | በበጀት ዓመቱ ከተቋሙ የለቀቁ | | | አሁን በሥራ ላይ ያሉ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ |
| 1 | 1ኛ-12ኛ | 16 | 20 | 36 | 1 | 2 | 3 | 1 | - | 1 | 16 | 22 | 38 |
| 2 | TVT (Level) | 6 | 13 | 19 | - | - | - | - | - | - | 6 | 13 | 19 |
| 3 | ዲኘሎማ (10+3) | 4 | 7 | 11 | - | 2 | 2 | 1 | - | 1 | 3 | 9 | 12 |
| 4 | ቢ.ኤ/ቢ..ኤስ.ሲ ዲግሪ | 67 | 42 | 109 | 2 | 3 | 5 | 2 | 1 | 3 | 67 | 44 | 111 |
| 5 | ኤም.ኤ/ኤም.ኤስ.ሲ ዲግሪ | 18 | 5 | 23 | - | - | - | 1 | - | 1 | 17 | 5 | 22 |
| 6 | ፒ.ኤች.ዲ | 2 | - | 2 | - | - | - | 1 | - | 1 | 1 | - | 1 |
| ድምር | | 113 | 87 | 200 | 3 | 7 | 10 | 6 | 1 | 7 | 110 | 93 | 203 |

**ማስታወሻ**

በኢቴኢ ከኳሊቲ ኢንጀነሪንግ ማዕከል ወደ በኢንስቲትዩታችን በጊዜያዊነት ተመድበው ከመጡ ሠራተኞች ዉስጥ ቋሚ ምደባ ያላገኙ ነገር ግን እየሠሩ ያሉትን 31 (ወ=23, ሴ=8) ጨምሮ እንዲሁም በተቋሙ በኮንትራት የተቀጠረ ወንድ ሹፌር 1 በአጠቃላይ የኢንስቲትዩታችን ሠራተኞች ብዛት 234 (ወ=133, ሴ=101) ናቸው፡፡

| 7. የ2016 በጀት ዓመት የዓመቱ የፋይናንስ አፈጻጸም | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | በ2016 በጀት ዓመት የፋይናንስ ዕቅድ | በ2016 በጀት ዓመት ጥቅም ላይ የዋለ/ወጪ | የ2016 በጀት ዓመት የዓመቱ የፋይናንስ አፈፃፀም ከዓመቱ ዕቅድ ጋር ሲነጻጸር | |
| | | ከመንግስት | ከውጭ እርዳታ | |
| መደበኛ በጀት | | | | |
| ፕሮግራም 01 | 33,943,398.50 | 32309992.73 | | 95.2 |
| ፕሮግራም 02 | 8,879,998.00 | 8,617,209.88 | | 97 |
| ፕሮግራም 03 | 12,735,820.74 | 11,897,802 | | 93.4 |
| ፕሮግራም 04 | 9,488,942 | 8,368,779.52 | | 88.1 |
| ንዑስ ድምር | 65,048,159.00 | 61,193,784.13 | | 94 |
| ካፒታል በጀት | | | | |
| ድምር | 65,048,159.00 | 61,193,784.13 | | 94 |

## 8. ማጠቃለያ

የ2016 በጀት ዓመት ዕቅድ ሲዘጋጅ መሰረት ያደረገው የኢንስቲትዩቱን የ10 ዓመት መሪ ዕቅድ እና የ3 ዓመት የመካከለኛ ዘመን የልማት ዕቅድ (2016-2018) መሰረት በማድረግ ፤የኢንስቲትዩቱን ጥንካሬ፣ ድክመት፣ መልካም አጋጣሚ ፣ ስጋትን በመተንተን እንዲሁም 11 ስትራቴጂያዊ ግቦችን በማካተት፣ የ2016 በጀት ዓመት የመጀመሪያውን 6 ወራት የዕቅድ አፈጻጸም በመገምገም በዋና እና ዝርዝር ተግባራት ተለይቶ የ2016 በጀት ዓመት ዕቅድ ተከልሶ ወደ ትግበራ ተገብቷል፡፡

በመሆኑ ከዓለም አቀፍ ሥነ-ልክ ስርዓት ጋር የተጣጣመ የኢትዮጵያ ሥነ-ልክ ስርዓትን ለመዘርጋትና ተግባራዊ ለማድረግ 232 (ወ=136, ሴ=96) ሠራተኞችን ይዞ ቀሪውን በጀት ዓመት ዕቅድ በተጠናከረ መልኩ ለማከናወን ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡ በመሆኑም በ2016 በጀት ዓመት የተከናወኑ የዋና ዋና ተግባራት ማጠቃለያ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የደንበኛ /የባለድርሻ እርካታ ከማሳደግ አንጻር ለ24854 የመለኪያ መሳሪያዎች የካሊብሬሽን አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡ ለ254 ከተቋማት አቅም በላይ ለሆኑ የሳይንስ መሳሪያዎች የጥገና አገልግሎት እና ለ18 የህክምና መሳሪያዎች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ተሰጥቷል፡፡

በሥነልክ ዘርፍ የኢትዮጵያ የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን፣ ለኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ባለሙያዎች ፣ ከሱማሊላንድ የጥራት ቁጥጥር ኮሚሽን ለመጡ የስነ-ልክ ባለሙያዎች እና ለኢትዮጵያ የኮንስትራክሽን ዲዛይንና ሱፐርቪዥን ሥራዎች ኮርፖሬሽን ምርምር ላቦራቶሪና ስልጠና ባለሙያዎች በተለያዩ በሥነልክ ርእሶች ላይ ለ76(ወ=49 ,ሴ=27) ባለሙያዎች የጽንሰ ሃሳብና የተግባር ስልጠናዎች ተሰቷቸዋል፡፡ እንዲሁም በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፍ ከፊስቱላ ሆስፒታል ፣ ከአዲስ አበባ ጤና ቢሮ እና ከኢሥኢ ለተውጣጡ ባለሙያዎች 13(ወ=10 ,ሴ=3) ሁለት የሥልጠና ኮርሶች ላይ ስልጠና በተከታታይ ተሰጥተዋል፡፡

ሥነልክ ዘርፍ ለኢትዮጵያ የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን፣ለ ODO International Export ድርጅት እና በሳይንስ መሳሪዎች ዘርፍ ለኦሮሚያ ግብርና ግብዓቶች ቁጥጥር ባለሥልጣን እንዲሁም ለኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የሶላር ፓነል ሲስተም የምክር አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡

ተደራሽነትን ከማሳደግ አንጻር ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ለህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ፣ ለኦሮሚያ ምርጥ ዘር ኢንተርፕራይዝ እና ለእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት የቴክኒክ ድጋፍ ተሰጥቷል፡፡ አዲስ እየተሰራ ያለውን ድረ ገጽ ተጠናቆ ስራ ላይ ውሏል ኢንስቲትዩቱን በሚመለከት ለድረ-ገጽ የሚመጥኑ መረጃዎችን በማዘጋጀት እና በመጫን ወቅታዊ እንዲሆኑ የተደረገ ሲሆን ከአራቱ የጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት ጋር በመተባበር በጋራ ለአምራችና ኢንዱስትሪዎች እንዲሁም ለአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ለ50(ወ=45 ሴት5) ሠልጣኞች በጅማ እና በድሬደከተማ የግንዛቤ ማስጨበጫ ተሰጥቷል፡፡

ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ከማሳደግ አንጻር በጀርመን የስነ-ልክ ኢንስቲትዩት ኢትዮጵያ ካለው ፕሮጀክት ድጋፍ የዳይሜንሽናል እና የግፊት ብሔራዊ የመጀመሪያ ደረጃ የማነጻጸሪያ መለኪያ መሳሪያዎች የዕርከን ተዋረድ ትስስር ማስጠበቅ ተችሏል፡፡

በግዝፈት፣ በሙቀት፣ በሚዛን፣ በኃይል፣ በዳይሜንሽናል፣ በጊዜና ድግግሞሽ የመጀመሪያ ደረጃ ብሔራዊ የማነጻጸሪያ ስታንዳርዶች በደቡብ አፍሪካ የሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት የዕርከን ተዋረድ ትስስር ማስጠበቅ ተችሏል፡፡ እንዲሁም በዋናው መስሪያ ቤት እና በደንበኞች የካሊብሬሽን ላቦራቶሮች ለሚገኙ ሁለተኛ ምድብ ማነጻጸሪያ መለኪያ መሳሪያዎች ዓለም አቀፍ የዕርከን ተዋረድ ትስስር ለ290 የሁለተኛ ምድብ የዕርከን ተዋረድ ስርጭት ተከናውኗል፡፡

**የአለካክ ወሰኖችን ከማሳደግ አንጻር** በጥራት መሰረተ ልማት ፕሮጀክት ድጋፍ ከደቡብ አፍሪካ የስነ-ልክ ኢንስቲትዩት በመጡ ባለሙያ በ ISO 17034 የማመሳከሪያ ስረት አመራረት ላይ ለኢንስቲትዩቱ የኬሚካል ሥነ-ልክ ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ እንዲሁም በጀርመን የሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት /PTB/ በተደረገ ድጋፍ አራት የኢንስቲትዩታችን ባለሙያዎች ለሶስት ወር በፎቶሜትሪ፣ ራዲዮሜትሪና ከለሮሜትሪ የአለካክ መስኮች በስፔክትሮፎቶ ሜትር ላይ በዶ/ር ፍራንዝ ስልጠና ወስደዋል፡፡

**የሰው ሀብት ልማት ከማልማት አንጻር** በተለያዩ የስልጠና ዘርፎች 151 (ወንድ= 111 ሴት= 37) አመራሮችና ሰራተኞች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

**የሴክተር ዘለል ተግባራትን** በሚመለከት ኤች አይቪ በደማቸው ውስጥ ለሚገኝ የተቋሙ ሰራተኞች እና ወላጆቻቸውን ላጡ ሁለት ሕፃናት የኢንስቲትዩቱ ሠራተኞች ከደመወዛቸው ተቆራጭ በማድረግ 19495.70 ብር የገንዘብ ድጋፍ ተደርጓል፡፡ 13,000,000 የአገልግሎት ክፍያዎች ተሰብስቦ ለገ/ሚ ገቢ የተደረገ ሲሆን የ2016 በጀት ዓመት የተግባራት አፈጻጸም 86% ሲሆን የበጀት አፈጻጸሙ 94% ሆኗል፡፡

## 9. የ2016 በጀት ዓመት የዋና ዋና ግቦች አፈፃፀም በሠንጠረዥ

| ተ.ቁ | የዋና ዋና ግቦች አፈጻጸም በሰንጠረዥ | የ2015 መነሻ | የ2016 ዕቅድ ኢላማ | የ2016 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም % |
| **ግብ 1** | **የደንበኛ /የባለድርሻ እርካታ ማሳደግ** | | | | | |
| 1.1 | **ጥናትና  ምርምር ማካሄድ** | | | | | |
| 1.1.1 | **2 ጥናትና ምርምር ማካሄድ** | **4** | **2** | **2** | 2 | 100 |
| 1.2 | **የካሊብሬሽን አገልግሎቶች መስጠት** | | | | | |
| 1.2.1 | የካሊብሬሽን አገልግሎቶች መስጠት | 27390 | 31000 | 31000 | 24854 | 80.2 |
| 1.3 | **የጥገና አገልግሎቶች መስጠት** | | | | | |
| 1.3.1 | ለ300 የሳይንስ መሳሪያዎች የጥገና አገልግሎት መስጠት | 252 | 300 | 300 | 254 | 84.67 |
| 1.4 | **የስልጠና አገልግሎቶች መስጠት** | | | | | |
| 1.4.1 | በሥነ-ልክ ዘርፍ እና በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፍ ሙያዊ ስልጠና መስጠት | **8** | **8** | 8 | 9 | 116.7 |
| 1.5 | **የምክር አገልግሎቶች መስጠት** | | | | | |
| 1.5.1 | በሥነ-ልክ ዘርፍ እና በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፍ የሚቀርቡ የአገልግሎት ጥያቄዎች 100% የምክር አገልግሎቶች መስጠት | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 1.6 | **የብቃት ማረጋገጥ አገልግሎቶች መስጠት** | | | | | |
| 1.6.1 | የህክምና መሳሪያዎች ተከላ፣ ጥገናና ኮሚሽኒንግ የብቃት ማረጋገጥ ለሚጠይቁ ደንበኞች ሙሉ በሙሉ አገልግሎት መስጠት | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 1.7 | የተጠቃሚ እርካታ ጥናት ማድረግ | | | | | |
| 1.7.1 | የተገልጋይ እርካታ መመዘን | 1 | 1 | 1 | 1 | 100 |
| **ግብ 2** | ተደራሽነትን ማሳደግ | | | | | |
| 2.1 | በቅርንጫፍ ካሊብሬሽን ላብራቶሪዎች የአገልግሎት ወሰን ማስፋትና ማስቀጠል | | | | | |
| 2.1.1 | በጅማ ቅርንጫፍ ካሉብሬሽን ላብራቶሪዎች በሙቀት አለካክ መስክ የአገልግሎት ወሰን ለማስፋት የላብራቶሪ መሣሪያ ግዥ ማጠናቀቅ | 0 | 1 | 1 | 0.5 | 50 |
| 2.2 | **የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት** | | | | | |
| 2.2.1 | የጥገና ወርክሾፕ እና የካሊብሬሽን ላቦራቶር ለማቋቋም ጥያቄ ለሚያቀርቡ የግል ባለሃብት፣ አምራችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የቴክኒክ ድጋፍ አገልግሎት መስጠት | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 2.3 | **የኢንስቲትዩቱ ዌብሳይት ለጎብኚዎች ምቹ እንዲሆን ማድረግ** | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 2.3.1 | ኢንስቲትዩቱን በሚመለከት 12 ለድረ-ገጽ የሚመጥኑ መረጃዎችን ማዘጋጀትና መጫን | 12 | 12 | 12 | 12 | 100 |
| 2.3.2. | የMet/Team ሲስተምን ተግባራዊ በማድረግ የካሊብሬሽን ደንበኞችን የመረጃ አያያዝ አውቶሜት በማድረግ ከደንበኞች አገልግሎት እስከ ፈጻሚዎች ያለውን የመረጃ ልውውጥ ማዘመንና ደንበኞች ባሉበት ሁነው ስራቸው የት እንደደረሰ ክትትል የሚያደረግጉበት ሲስተም ተግባራዊ ማድረግ | 0 | 3 | 3 | 1.5 | 100 |
| 2.4 | **የግንዛቤ ማስጨበጫ መስጠት** | | | | | |
| 2.4.1 | በተመረጡ አካባቢዎች (አርባ ምንጭ፣ጅማ፣ እና አሶሳ) የግንዛቤ ማስጨበጫ መስጠት | 6 | 3 | 3 | 2 | 66.6 |
| ግብ 3 | የበጀት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ | | | | | |
| 3.1 | **የበጀት አጠቃቀምን መከታተል** | | | | | |
| 3.1.1 | የፀደቀውን በጀት በእቅዱ መሰረት 100% መጠቀም | 95.5 | 100 | 100 | 94 | 94 |
| 3.2 | **የአገልግሎት ክፍያዎችና ተሰብሳቢ ሂሳቦች በወቅቱ ለመንግስ<br>ት ገቢ ማድረግ** | | | | | |
| 3.2.1 | የአገልግሎት ክፍያዎችና ሌሎች ገቢዎችን በማስገባት በወቅቱ ለመንግስት ገቢ ማድረግ | 12 ሚሊዮን | 13 ሚሊዮን | 9,750,000 | 9,332,478.369 | 95.72 |
| 3.3 | **የፋይናንስ ኦዲት ማከናወንና መከታተል** | | | | | |
| 3.3.1 | አምስት/5/ የሂሣብ ኦዲት ሪፖርት ማዘጋጀት | 5 | 5 | 4 | 4 | 100 |
| 4 | የፋይናንስ ምንጮች ማበራከት | | | | | |
| 4.1 | ፕሮጀክቶች በማዘጋጀት ድጋፍ መጠየቅ | 0 | 1 | 1 | 1 | 100 |
| ግብ 5 | **አለም አቀፍ ተቀባይነት ማሳደግ** | | | | | |
| 5.1 | ዓለም ዓቀፍ እርከን ተዋረድ ትስስር መጠበቅና ማሰራጨት | | | | | |
| 5.1.1. | በግዝፈት፣ በሙቀት፣ በዳይሜንሽናል፣ በጊዜና ድግግሞሽ እና በግፊት አለካክ መስኮች ብሔራዊ የመጀመሪያ ደረጃ የማነፃፀሪያ መለኪያ መሣሪያዎችን ዓለም አቀፍ የዕርከን ተዋረድ ትስስር መጠበቅ፣ | 4 | 5 | **5** | 2.5 | 50 |
| 5.1.2 | 182 ሁለተኛ ምድብ ማነጻጸሪያ መለኪያ መሳሪያዎች ዓለም አቀፍ የዕርከን ተዋረድ ትስስር ማሰራጨት | 214 | 232 | **182** | 173 | 95 |
| 5.2 | **ዓለም አቀፍ እውቅና የተገኘባቸው የአለካክ መስኮች/ወሰን ማስቀጠል** | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 5.2.1 | በላቦራቶሮች ህንጻ ለውጥ ምክንያት ዓለም አቀፍ ዕውቅናቸው በፈቃደኝነት የታገዱት የውስጥ ላቦራቶር (የግዝፈት፣ የኤሌክትሪካል፣ የሙቀት፣ የግፊትና የይዘት) የአለካክ መስኮች እንደገና ዓለም አቀፍ ዕውቅና ለማግኘት ማደራጀትና ዝግጁ ማድረግ፣ | 0 | 5 | **5** | 0 | 0 |
| 5.2.2 | ዓለም አቀፍ ዕዉቅና በነበራቸዉ የውስጥ ካሊብሬሽን(የግዝፈት፣ በኤሌክትሪካል፣ በሙቀት፣ ግፊትና በይዘት (5)፣ በተንቀሳቃሽ (4) እና በመስክ (2) የካሊብሬሽን የአለካክ መስኮች ዓመታዊ የውስጥ የጥራት ኦዲት ማከናወን፣ | 0 | 5 | **5** | 0 | 0 |
| 5.2.3 | በሀዋሳ ቅርንጫፍ ላቦራቶሪዎች ዕውቅና ባልተገኘበት በሚዛን ካሊብሬሽን አገልግሎቶች በውስጥ ባለሙያ አለም አቀፍ እውቅና ለማግኘት | 0 | 2 | **2** | 2 | 100 |
| 5.3 | **በአዳዲስ የአለካክ መስኮች/ወሰን እውቅናን ማስፋት** | | | | | |
| 5.3.1 | በወበቅ (Humidity)፣ በእርጥበት (Mositure) እና በኃይል (Force) የአለካክ መስኮች የካሊብሬሽን የአሰራር ስርዓት ሰነድ ማዘጋጀት | 0 | 3 | **3** | 2.25 | 75 |
| 5.3.2 | በዳይሜንሽናል አለካክ መስክ ዓለም አቀፍ ዕውቅና ለማግኘት ስልጠናዎች ማግኘትና የካሊብሬሽን የአሰራር መመሪያዎች /Procedures/ መከለስ | 0 | 1 | **1** | 0 | 0 |
| 5.4 | በዓለም አቀፍ የሥነ-ልክ ድርጅት መረጃ ቋት BIPM-KCDB)ማስመዝገብ | | | | | |
| 5.4.1 | የሙቀት እና የይዘት የካሊብሬሽን ልኬት ብቃት/CMC/ በዓለም አቀፍ የሥነ-ልክ ድርጅት መረጃ ቋት /BIPM-KCDB/ እንዲመዘገብ ክትትል ማድረግ፣ | 0 | 2 | **2** | 1 | 75 |
| 5.4.2 | ዓለም አቀፍ ዕውቅና ያላቸው የአለካክ መሰኮች የካሊብሬሽን ልኬት ብቃታቸውን /CMC/ በዓለም አቀፍ የሥነ-ልክ ድርጅት መረጃ ቋት /BIPM-KCDB/ ለማስመዝገብ በሂደት ላይ ያሉ እና አዳዲስ የላቦራቶሮች ቁልፍና ድጋፍ ንጽጽር ፕሮግራሞች መከታተልና መሳተፍ፣ | 0 | 1 | **1** | 1 | 100 |
| 5.5 | ከአህጉራዊና ዓለምአቀፍ የሥነልክ ተቋማት ጋር ተሳትፎ ማድረግ | | | | | |
| 5.5.1 | በአህጉራዊ AFRIMET እና NEWMET ዓመታዊ የቴክኒካል ስብሰባዎች ላይ መሳተፍ እና የንጽጽር ፕሮግራሞችን ማመቻቸት | 0 | 1 | **1** | 1 | 100 |
| 5.6 | **የጥራት ስራ አመራር ስርዓቶችን በመለየት ተግባራዊ ማድረግ** | | | | | |
| 5.6.1 | ( ISO 9001:2015) ተግባራዊ ለማድረግ ለስራ አመራር አባላት እና ለሚመለከታቸው ባለሙያዎች በኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት ስልጠና መስጠት | 0 | 1 | **1** | 0.5 | 50 |
| **ግብ 6** | **የአለካክ ወሰኖችን ማሳደግ** | | | | | |
| 6.1 | **የአለካክ መስክ/ወሰን ማሳደግ** | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 6.1.1 | **በግዝፈት የአለካክ መስክ የልኬት ትክክለኝነት አሁን ካለበት ከ E2 ወደ E1/E0 ደረጃ ለማሳደግ ስልጠናዎችን በመውስድ ቅደመ ዝግጅት ማጠናቀቅ፣** | 0 | 1 | 1 | 1 | 100 |
| 6.1.2 | በኬሚካል ሥነ-ልክ፣ በፎቶሜትሪና ራዲዮሜትሪ እንዲሁም በጊዜና ድግግሞሽ የአለካክ መስኮች በስፔክትሮፎቶ ሜትር አለካክ መስክ የካሊብሬሽን አገልግሎት ለማስጀመር የሚያስችል ስልጠናዎችን በማግኘት ላቦራቶሮችን ማደራጀት | 0 | 3 | 3 | 3 | 100 |
| ግብ 7 | **አሰራር ቅልጥፍናን ማሻሻል** | | | | | |
| 7.1 | የተሻሻሉና አዳዲስ ኦላይን ሲስተሞች ተግባራዊ ማድረግ | | | | | |
| 7.1.1 | የሳይንስ መሳሪያዎች የብቃት ማረጋገጫ አገልግሎትን አውቶሜት በማድረግ ተጠቃሚዎች ባሉበት ሆነው ማመልከት እንዲችሉ እንዲሁም ክትትል ማድረግ የሚያስችል አገልግሎትን ማስጀመር | 0 | 1 | 1 | 0.90 | 90 |
| 7.1.2 | በተቋሙ ተግባራዊ የተደረጉ የደንበኞች አገልግሎት ሲስተሞችን ተፈጻሚነት ለማዝለቅ ድጋፍና ክትትል ማድረግ | 0 | 4 | 3 | 3 | 100 |
| 7.2 | **ደንቦች፣ መመሪያዎችና ውሎች ማዘጋጀትና መከለስ** | | | | | |
| 7.2.1 | በኢንስቲትዩቱ የሚቀርቡ የፍትሐብሄር ጉዳዮችን ማቅረብ፣ መከራከር መከታተልና የኢንስቲትዩቱን ጥቅም በህግ አግባብ ማስጠበቅ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 7.2.2 | ተዘጋጅተው የሚቀርቡ ረቂቅ የህግ ማእቀፎችን ቅርጽና ይዘት ማስጠበቅና አስፈላጊውን ክትትል ማድረግ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 7.2.3 | በሚቀርቡ የህግ ጉዳዮች አስተያየትና የማማከር አገልግሎት መስጠት | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 7.3 | **የአገልግሎት ፣የመሳሪያ ግዢ እና የአባልነት ክፍያ መፈጸም** | | | | | |
| 7.3.1 | በግዥ ዕቅዱ መሠረት ግዥ መፈፀም | 1 | 2 | 2 | 1.66 | 83 |
| 7.4 | ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ማከናወን | | | | | |
| 7.4.1 | የንብረት ቆጠራ ማካሄድ እና ስራ ላይ የማይውሉ ንብረቶችን በወቅቱ ማስወገድ | 1 | 1 | 1 | .8 | 80 |
| | | 1 | | 1 | 1 | |
| ግብ 8 | **ቅንጅታዊ አሰራር ማሻሻል** | | | | | |
| 8.2 | **ከአቻ የውጪ የሥነ-ልክ ተቋማት ጋር በትብብር መስራት** | | | | | |
| 8.2.1 | 1 ከጀርመን (PTB)፣ከደቡብ ኮርያ (KRISS)፣ከደቡብ አፍሪካ (NMISa)፣ ከቱርክ (UME)፣ ከሶማሌላንድ (SQCC) ሥነ-ልክ ተቋማት ጋር አብሮ መስራት የሚያስችሉ የአሰራር ዘዴዎች በማጥናት ተግባራዊ | 3 | 5 | 2 | 3 | 100 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ለማድረግ | | | | | |
| 8.3 | **ከጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት ጋር በትብብር መስራት** | | | | | |
| 8.3.1 | ከጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት ጋር በትብብር መስራት | 2 | 2 | 1 | 1 | 100 |
| **ግብ 9** | የሰራተኛውን ብቃት ማሳደግ | | | | | |
| 9.1 | **የሰው ሀብት ልማት ማልማት** | | | | | |
| 9.1.1 | ለሠራተኞች ስልጠና መስጠት | 180 | 200 | 175 | 151 | 86.3 |
| 9.1.2 | ሁለተኛ እና ሶስተኛ ዲግሪ የትምህርት ዕድል መስጠት | 3 | 2 | 2 | 2 | 100 |
| 9.2 | **የሴቶችን ተሳትፎ ለማሳደግ ስልቶችን መቀየስ፣፣ መከታተልና ማጠናከር** | | | | | |
| 9.2.1 | ኤች አይቪ በደማቸዉ ዉስጥ ለሚገኝ ሁለት የኢንስቲትዩቱ ሠራተኞችና ወላጆቻቸዉን ላጡ ሁለት ሕፃናት ድጋፍ ማድረግ | 20694 | 21600 | 18000 | 16451.34 | 91.4 |
| 9.2.2. | የስርዓተ ጾታ ጋድላይን አፈጻጸም ተግባራዊነት ክትትልና ድጋፍ ማድረግ | 4 | 4 | 3 | 3 | 100 |
| 9.3 | **የተቀናጀ የሙስናና የመከላከል ስትራቴጂ ተግባራዊ ማድረግ** | | | | | |
| 9.3.1. | በተቋም ለሙስና ተጋላጭነት ስጋት በሆኑ አሰራሮች ላይ የተደረገውን ጥናት ተግባራዊ ማድረግ | 1 | 1 | 1 | 0.7 | 70 |
| 9.3.2. | የተቋሙ የሥነ-ልክ ባለሙያዎች ሀብታቸውን እንዲያስመዘግቡ ማድረግ | 80 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| **ግብ10.** | የስራ አካባቢና መሰረተ ልማት ማሻሻል | | | | | |
| 10.1 | የአካባቢ ብክለትንና በህብረተሰቡ ጤና ጉዳት መቀነስ | | | | | |
| 10.1.1. | የሁለተኛ ምድብ የጨረራ ላቦራቶር/SSDL/ ጨረር ልቀት መቆጣጠርና በአከባቢው የሚያመነጨውን መጠን በየጊዜው በመከታተል ሪፖርት ማቅረብ | **1** | **4** | **3** | **3** | 100 |
| 10.2. | ተስማሚ የሆኑ የሥራ ቦታዎች ማዘጋጀት | | | | | |
| 10.2.1 | የጠቅላላ አገልግሎት ስራ ተግባራዊ ማድረግ (ግቢ ውበት፣ፋሲሊቲ እና እድሳት) | | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 10.3. | **የኢ/ኮ/ቴ መሠረተ ልማት ደህንነትና ወቅታዊነት ማስጠበቅ** | | | | | |
| 10.3.1 | በተቋሙ ተግባራዊ የተደረጉ ልዩ ልዩ ሲስተሞችን (ኢፍሚስ፤ ኢጂፒ፤ ኢስሚስ፤ ኢሜል፤ ዌብሳይት) ደህንነት መጠበቅና ለተጠቃሚዎች የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት | 1 | 4 | 3 | 3 | 100 |
| 10.3.2 | ለአዳዲስ የኢኮቴ መሰረተ ልማቶችን (ዌብፖርታል፤ የጥገና፤የካሊብሬሽን፤የሰርተፊኬሽን አገልግሎቶች) | 1 | 4 | 3 | 3 | 100 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ተጠቃሚዎች  የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት | | | | | |
| 10.4 | **የለውጥና መልካም አስተዳደር የአሰራር ስርዓቶች መዘርጋት** | | | | | |
| 10.4.1 | ተቋማዊ ለውጥ ላይ የማሻሻያ ሀሳብ ዶክመንት ማቅረብ | 1 | 1 | 1 | 1 | 100 |
| 10.4.2 | የውስጥ፣ የውጭ ቅሬታና አስተያየት በመቀበል እንዲፈቱ ለሚመለከተው ማቅረብና እርምጃ ማስወሰድ | 0 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| **ግብ 11** | የክትትልና የግምገማ ስርዓትን ማሻሻል | | | | | |
| 11.1 | ፕሮጀክቶችን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ | | | | | |
| 11.1.1 | ግንባታቸው ባለቀ ወይም በከፊል አልቀው ስራ እንዲጀምርባቸው የተወሰኑ ላብራቶሮችን ወርኪግ ቤንቾች እና ሌሎች አስፈላጊ ፋሲሊቲዎች የማሟላት ስራዎችን መከታተልና መደገፍ | 4 | 4 | 3 | 3 | 100 |
| 11.2 | የውጤት ተኮር ዕቅድ ማዘጋጀትና  አፈጻጸም መገምገም | | | | | |
| 11.2.1 | የውጤት ተኮር ዕቅድ ማዘጋጀት፣ በየደረጃው መፈራረም ፣ በየወሩ አፈጻጸም መገምገም እና ምዘና ማካሄድ | 1 | 2 | 2 | 2 | 100 |